# የቅድስና በዓልን ማክበር

## የትንንሽ ቡድኖች አጀማመር

## የአፍርካ ናዛሪን ቤተ ክርስቲያን

Web site: www.africanazarene.org

### ትንንሽ ቡድኖች ምን ማለት ነው

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ የትንንሽ ቡድን የሚያመለክተው ከ3-12 ሰዎች ብዙ ጊዜ ክርስቶስን በማወቅና በመከተል ለማደግ ዓላማ የሚሰባሰቡበት ነው። የቡድኑ ዓላማ የቡድኑን ባሕርይ፣ አባላት እና በቡድኑ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ይወስናል።

### ዓላማው ምንድ ነው

የቤተ ክርስቲያኗ አባላት በትንንሽ ቡድኖች ለመጸምና ለመጸለይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አብሮ ለማጥናት እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን እና ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት አንዱ አንዱን እንድቆጣጠር ይሰባሰባሉ።

በትንንሽ ቡድኖች ሆነው ‹‹የቅድስናን በዓል›› የማክበር ትልቁ ጠቀሜታ ይህ ቡድኑ በቀጣይነት ቅዱስ ሕብረት፣ ሙሉ ለሙሉ የተቀደሰ፣ በቅድስና ላይ የተገነባ እንዲሁም በቀደምት የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመበረውን መንፈሳዊ ኃይል ለመፈለግ ስለሚረዳ ነው። (*መምሪያ 2009-2013*, ¶25).

### ትንንሽ ቡድኖችን እንዴት እንጀምር

- በተገለጸው ዓላማ መሠረት መጀመር የምትፈልጉትን ቡድን ባሕርይ ወስኑ
  - የጸሎትና የጾም፣ የመጸሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የቃል ኪዳን ወይስ አንዱ ለአንዱ ተጠያቂ የሚሆንበት ቡድን ነው መጀመር የሚትፈልጉት?
  - የዚህ ቡድን አባላት የሚሆኑን እነማን ናቸው? ሁሉም ሰው የዚህ ቡድን አባል መሆን ይችላል ወይስ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ናቸው? በቡድኑ ውስጥ የሚታቀፉት ሰዎች ብዛት እና የሰዎቹ ማንነት የቡድኑን የቅርርብ መጠን እና ግልጽነት ይወስነዋል።
  - ይህ ቡድን ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል?
  - ቡድኑ ስገናኝ በአንድነት የሚያሳልፈው ጊዜ ምን ያህል ነው? 1-1½ ሰዓት ቢሆን ይመከራል።
- መጀመር የሚትፈልጉትን የትንነሽ ቡድኖች መጠን ወስኑ
  - በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ በአሁን ወቅት ምን ያህል ትንንሽ ቡድኖች እንዳሉ ወስኑ።
  - ዬት እንደሚገኙ፣ አቅማቸው ምን ያህል እንደሆነና ግባቸው ላይ ለመድረስ ያላቸው ውጤታማነት ምን ያህል እንደሆነ አጥኑ
  - ይህንን እድል እንደገና ለመጀመር ጥሩ እድል እንደሆነ ቁጠሩት

- በቤተ ክርስቲያናችሁ ትክቅነት መጠን እና ባላችሁ የተሰጡ መሪዎች መጠን ከአንድ ቡድን ይልቅ ከሦስት እስከ አራት ቡድን ቢኖር ይመከራል፡፡

➢ ቡድኑ ከግቡ እንድደርስ የሚያግዙ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን መሰብሰብ

- ሁሉም ቁሳቁሶች በጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት መጋበው ዘንድ መቅረብ እና ማረጋገጫ ማግኘት አለባቸው

➢ የቡድን ስብሰባው ዬት ቤት እንደሚደረግ፣ ረዳት መሪዎች እነማን እንደሆኑ ወዘተ መዝግቡ፡፡ ስብሰባው በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ የሚደረግ ከሆነ የቡድኑ መሪ እንዲሆኑ አይመከርም፡፡

➢ ስብሰባው የሚካሄድበትን ቦታወስኑ እንዲሁም ቦታውን ለመጠቀም አስፈላጊውን ዝግጅት ሁሉ አድርጉ

➢ ስለ ቡድን ስብሰባው ማስታወቂያ ንገሩ እንዲሁም ሰዎችን ወደ ስብሰባው ጋብዙ፡፡ ሰዎችን ስትጋብዙ ከቦታው፣ ከሰዓቱ፣ ከመሪዎቹ እና አባላቱ በተጨማር የስብሰባው ዓላማ ምን እንደሆነ በተቻላችሁ መጠን ግለጹ፡፡

- በስብሰባው ውስጥ አባል ለመሆን የሚያስፍልገው መስፈረት

  -ለቅድስና ያለው ረሃብና ጥማት

  -በተባለው ሰዓት ሁል ጊዜ ለመገኘት ያለው ቁርጠኝነት

  -በትንንሽ ቡድን ውስጥ ተሳርፎ በማድረጉ የሚያገኘውን ጠቀሜታ ጥንቅቆ የሚያውቅ:

  - ክርስቶስን ለመመስል የሚያግዘው ተግባራዊ ትምህርት የሚያገኝበት
  - ለሌሎች ተጠያቂ የሚሆንበት ሥፍራ በመሆኑ ለመንፈሳዊ እድገት እና ይበልጥ ክርስቶስን ለመምሰል የሚረዳ መሆኑ
  - በይተዋር አለመሆን

➢ የዚህ ቡድን አባል መሆኛ መስፈርት አንድ ጊዜ ከተወሰነ በኋላ ግልጽ የሆነ ቃል ኪዳን እና እርስ በእርስ የመያያዣ፣ አንዱ ለሌላኛው ተጠያቂ የሚሆንትን መንገድ ማመቻቸት

### የትንንሽ ቡድን መሪዎች የሥራ ኃላፊነት

➢ ስብሰባውን ለማሳለጥና ቡድኑ ከግቡ ለመድረስ በትክክለኛ ጎዳና ላይ እየተጓዘ እነደሆነ ለማረዳገጥ መሪዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ኃላፊነታቸውም ከዚህ በታች የተዘረዘረውን ያካትታል:

- አስቀድሞ እቅድ ማውጣት
- በመሪሃ ግብሩ መሠረት መሥራት

- ለተሳታፊዎቹም ሆነ ስበሰባው በቤታቸው ውስጥ እንዲካሄድ የፈቀዱ ሰዎችን ላለማስቸገር ስበሰባውን ሁል ጊዜ በሰዓት ጀምሮ በሰዓት መጨረስ

➢ የቡድን ስብሰባውን ለማሳለጥ የሚያስፍለገው ልምድና ችሎታ እነዚህ ያጠቃልላል፡

- ሰዎችን በፍቅር መቀበል። ሁሉንም አባላት ክርስቶስ እንዳደረገው በሁኔታዎች ያልተገደበ ፍቅር በማሳየት ተቀበል
- በርኅራሄ አድምጥ እንዲሁም ምላሽ ስጥ። ተናጋሪው የሚናገረውን ነገር ሙሉ ለሙሉ እንደሰማ እና በትክክል እንደተረዳኸው አረጋግጥለት።
- ሰዎች እንድያግዙ ጠይቅ። ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ከሌለህ እንደማታውቀው በመግለጽ የቡድኑ አባላት ያግዙ ዘንድ ጠይቅ።
- የቡድኑ አባላት እንዲያስቡ እና እንዲወያዩ የሚያደርጋቸውን ዓይነት የአጠያየቅ ዘዴን ተማር። መማን፣ እንደ ማን፣ ምን፣ መቼ፣ ለምን፣ ዬት እና እንዴት በሚሉ ቃላት የሚጀምሩ ጥያቄዎችን ጠይቅ። የቡድኑ አባላት መልስ እስክሰጡህ ድረስ ጠበቅ። ከቡድኑ አባላት መካከል ለጥያቄው መልስ መስጠት የማይችሉትን እንዳታሳፍር ተጠንቀቅ።

➢ የተለያዩ ስብእና ያላቸው ሰዎች ለመውቀስ፣ ከመስመር የሚወጡ ሰዎችን ለመመለስ፣ ለጸሎት የሚቀርብ ሀሳብ በሚመስል መልኩ የሚመጡ ሀሜቶችን የመቆታጠር ክህሎትን አዳብር። ሁሉንም አስቸጋር ነገሮች በጥበበት ለመፍታት ሞክር።

➢ ቡድኑ ቀጣይነት እንዲኖረውና ከግቡም በአግባቡ መድረስ እንድችል በእግዚአብሔር ላይ ታመን። አቅድ ነገር ግን እግዚአብሔር የራሱን መንገድ እንድጠቀም ፍቀድለት

## በትንንሽ ቡድኖች ውስጥ ምን ይደረጋል

➢ **ጾም እና ጸሎጽ**

- ***15 ደቂቄች፡*** መዝሙር መዘመር እና ለተመለሱ ጸሎቶች እግዚአብሔር ማመስገን፡፤ ሁል ጊዜ ከዚህ በኂላ ሰዎች የጸሎት ጥያቄያቸውን እንድያቀርቡ አድርጉ።
- ***15 ደቂቃዎች፡*** መጽሐፍ ቅዱስ አንብቡ ነገር ግን ወደ ጥናት ወይም ስብከት አትግቡ
- ***30 ደቂቃዎች***: በጸሎት እቅዱ መሠረተ የጸሎት ጥያቄዎችን ለሁሉም አካፍሉ ከዚያም ከቡድኑ ጋር በጸሎት ለተወሰነ ጊዜ አሳልፉ።

➢ **የመጸሐፍ ቅዱስ ጥናት**

- ***15 ደቂቃዎች***: በመዝሙር እና በጸሎት መጀመር

- *30 ደቂቃዎች፡* ለጥናት የተመረጠው የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል ማንበብ እና በጥያቄዎቹ መሠረት ውይይት ማድረግ። ለመረዳት መሞከር፣ ክፍሉ ምንድነው የሚለው፣ ምን ማለት ነው፣ እንዴት በዘመናችን ልተገባር ይችላል።
- *15 ደቂቃዎች፡* የግል የጸሎት ጥያቄዎችን መቀባበል።

➢ ***ቃል ኪዳናዊ እና እርስ በእርስ ተጠያቂ የሚኮንበት (ከእግዚአብሔር እና ከቤተ ክርስቲያን ጋር ባለን ግንኙነት)***

ከእግዚአብሔረወ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ለማድረግ ስፈለግም ትንንሽ ቡድን መመሥራት ይቻላል።

- ለትንሽ ጊዜ መዘመር እና በጸሎት መጀመር
- የተስማማችሁበትን ጥያቄ እርስ በእርስ መጠያየቅ ለምሳሌ
  - ነፍስህ በምን ሁኔታ ላይ ትገኛለች?
  - በመንፈሳዊ ነገር ለማድረግ ምን እያደረግህ ነው?
  - ባለፈው ሳምንት ውስጥ ሰዎችን ለማገልገል ምን አይነት እድል አግኝተህ ነበር፣ እነዴትስ ተጠቀምክበት?
  - ምን ዓይነት ፈተና ገጠህ እንዴትስ ተወጠኸው?
- በአጭሩ የጸሎት ርዕስ ተለዋወጡ።

*Developed by Rev Daphne Mathebula Africa Regional SDMI Coordinator*